የኤርትራ ተወላጆች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በረከት ስምኦንና መለስ ዜናዊ ወሰኑ፤

ነባር የሰራዊቱ አባሎችን የማባረሩ ዘመቻ ተጠናክሮ ቀጥሎዋል፤

መለስ ከቻይና ባለሀብቶች ጋር በምስጢር ከተፈራረማቸው ፋብሪካዎች መሀከል አንደኛው በይፋ ስራውን ጀመረ፤

በጅቡቲ ወደብ በተደረገው የታሪፍ ጭማሪ ነጋዴው ህብረተሰብ እየተማረረ መሆኑ፤

የሀገር ስጋት ናቸው በሚል ከኢትዮጵያ የተባረሩ የኤርትራ ተወላጆች ወደ ሀገር ቤት ገብተው መኖር እና ማናቸውንም እንቅስቃሴ ማድረግ ይችላሉ ሲል የወያኔ የሚኒስትሮች ምክር ቤት መወሰኑ ታወቀ::

ወያኔ ሰሞኑን ባወጣው በዚሁ መግለጫ ላይ እንደገለፀው ከሆነ የሀገር ስጋት ናቸው ተብለው የተባረሩ የኤርትራ ተወላጆች ወደ ሀገር ውስጥ መግባት የሚችሉ መሆኑንና በተጨማሪ ከሀገር ሰባረሩ በባንክ ውስጥ የነበራቸው ገንዘብም ሆነ ቋሚ ንብረት እንዲሰጣቸው እና እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ በንግድና በኢንቨስትመንት ስራ ላይ እንዲሳተፉ ሙሉ ነፃነት እንደተሰጣቸው ገልፆዋል::

የወያኔ ቡድን ርካሽ ተወዳጅነትንና እንዲሁም የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት እራሱ እየጠረዘ ያባረራቸውን የኤርትራ ተወላጆች መልሶ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ተመልሰው እንዲገቡ መወሰኑ ግራ ያጋባ ጉዳይ መሆኑን ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገልፀዋል::

በሻእቢያና በወያኔ መሀከል በተከሰተ ግላዊ ግጭት ምክንያት በአጭር ጊዜ በተደረገ ጦርነት ከሁለቱም ወገን ከ140 ሺህ ዜጎች በላይ ማለቃቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: ወያኔና ሻዕቢያ ለዘመናት ተፋቅሮ የኖረውን እና ተዋልዶ ያለውን ህዝብ እርስ በርስ እንዲጋጩ ከማድረጋቸውም በላይ ሁለቱም ከያሉበት እያባረሩ ለስደት መዳረጋቸው የወያኔ ቡድን ለሀገር ስጋት ናቸው በሚል ከኖሩበት ቦታ እየለቀመ ያባረራቸው ሲሆን ሻዕቢያም በበኩሉ ያለአንዳች ንብረት መለመላቸውን ማባረሩ የሚታወስ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

ወያኔ የሀገር ስጋት ናቸው በሚል ሲያባርራቸው አባትና እናት ከልጆቻቸው፤ ሚስት ከባልዋ፤እያለያየ እና እየነጣጠለ እንደነበረም የሚታወስ ሲሆን ሻዕቢያ በበኩሉ ለዘመናት በኤርትራ ውስጥ የኖሩትን ኢትዮጵያውያን ከያሉበት እየለቀመ ባዶ እጃቸውን ከማባረሩ ባሻገር የአንገት ሀብል፤የጋብቻ ቀለበት እንዲሁም ጥርሳቸው ላይ የተተከለ ወርቆችን ሳይቀር በጉጠት የነቀለና ያለ መጉዋጉዋዣ በእግራቸው በሺህ የሚቆጠር ኪሎ ሜትሮችን እንዲጉዋዙ ያስገደደ አረመኔ ቡድን መሆኑንና ዛሬ ወያኔ ይህን የመሰለ ውሳኔ ማሳለፉ ለህዝብ ያለውን ንቀት ያሳያል::

በአሰብ ወደብ ላይ በቢሊዮን ብር የሚቆጠር የኢትዮጵያውያን ንብረት በሻእቢያ ሲዘረፍ ትንፍሽ ያላለው ወያኔ ዛሬ ደርሶ ለኤርትራውያን አዛኝ መስሎ ይህንን ህግ ማውጣቱ የተለመደ የወያኔ ሽፍጥ እና ማጭበርበር ነው:: የሰሞኑን ውሳኔ ረቂቅ አዘጋጅተው ያቀረቡት በረከት ስምኦን እና መለስ ዜናዊ ሲሆኑ የኤርትራ ተወላጆች ሲባረሩም ትልቁን ድርሻ ሲወጡ የነበሩት እነዚሁ ግለሰቦች እንደነበሩና በተለይም መለስ

ዜናዊ የአይናቸው ቀለም ስላላማረኝ ይውጡ እያለ ሲደነፋ እንዳልነበር አሁን ደግሞ ግንባር ቀደም በመሆን ረቂቁን ሰርቶ ከማቅረብ ጀምሮ እስከ ማፀድቅ ድረስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተም ታውቆዋል::

በዚሁ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ የነበረው ይኸው ረቂቅ በራሳቸው በወያኔዎች ከፍተኛ አለመግባባትን ፈጥሮ እንደነበር ታውቆአል:: መለስ ዜናዊ እና በረከት ስምኦን ረቂቁን ከማዘጋጀታቸው በፊት የኦህዴድ ፤የደኢህዴን እና የብአዴን ከፍተኛ ባለስልጣናት እና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን በግል እየጠሩ የእነሱን አቁዋም እንዲደግፉ ያስፈራሩ መሆኑንና በውሳኔው ዕለትም ከብዙ ክርክር በሁዋላ በድምፅ ብልጫ እንዲወሰን መደረጉን ጥቆማው አብራርቶዋል::

በውሳኔው ላይም ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲፋጠን እና በአጭር ጊዜ እንዲከናወን ለማድረገው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ውስጥ አንድ መምሪያ ተቁዋቁሞ ስራውን እንዲጀምር የተደረገ ሲሆን መንግስታዊም ሆነ የግል ተቁዋማት ለተመላሾቹ አስፈላጊውን ትብብር እና ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስገድድ መመሪያ ውስጥ ውስጡን መተላለፉ ታውቆዋል::

አሁን በተሰጠው መመሪያና ትዕዛዝ መሰረት የቀድሞ ንብረታቸው ሙሉ ለሙሉ እንዲመለስላቸው እና በባንክ ውስጥ አስቀምጠውት የነበረው ገንዘብ እንዲመለስላቸው ከመወሰኑም በተጨማሪ ቀድሞ የቀበሌ ቤት የነበራቸውም በተመሳሳይ ተፈልጎ ምትክ እንዲሰጣቸው ምስጢራዊ ትዕዛዝ ተላልፉዋል:: ከ3 ዓመት በፊት ወደ ኤርትራ ተባረው ሄደው የነበሩና ወደ ኢትዮጵያ የተመለሱ ኤርትራውያን የመንግስት ስራዎቻቸው ላይ እንዲመለሱ ከመደረጋቸውም በላይ ያልሰሩበት የ5ዓመት እና ከዚያም በላይ የተጠራቀመ ገንዘብ እንደተከፈላቸው ይታወሳል:: በአሁን ሰዓት አዲስ የስራ ለውጥ በሚል ብዙ ዓመታት በመንግስት ስራ ላይ ሲሰሩ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በወያኔ አገዛዝ ከስራ በገፍ እየተባረሩ ነው::

የወያኔ ቡድን በነባር የሰራዊቱ አባሎች ላይ ባለው ጥርጣሬ የተነሳ በቅርቡ በሺህዎች የሚቆጠሩትን ከስራ ማባረሩ ታወቀ::በምስራቅ እዝ፤በሰሜን እዝ እና በምዕራብ እዝ ስር ይሰሩ የነበሩትን የጦሩ አባሎች የተለያየ ምክንያት እየሰጠ ከስራ ማሰናበቱን የመከላከያ ምንጮች ገልፀዋል:: በምስራቅ እዝ የተጀመረው የማባረር ዘመቻ በሰሜንና በምዕራብ እዞች ውስጥም ተስፋፍቶ የቀጠለ ሲሆን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሰራዊቱ አባላት እንደተቀነሱም ምንጮቹ አስረድተዋል:: ወያኔ በህዝብ እና በሀገር ላይ በሚሰራው በደልና ግፍ የተነሳ በሰራዊቱ ዘንድም ከዕለት ወደ ዕለት ቁጣንና ተቃውሞ በመቀስቀሱ በመደናገጥ ሰራዊቱን ያስተባብራሉ ብሎ የሚጠረጥራቸውን የጦር መኮንኖች እና ባለ ሌላ መዕረግ ከየጦሩ ክፍል እየለቀመ ለእስር ቢዳርግም ለውጥ ባለማግኘቱ

በጅምላ ከየጦሩ ክፍል በሺህዎች የሚቆጠሩትን ማባረር መጀመሩንና በየሔዱበት ችግር እንዳይፈጥሩ ለመቆጣጠር እንዲያመች ልዩ መታወቂያ የተሰጣቸው ሲሆን መደለያም የሚሆን የእርሻ መሬት እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል።

በተባረሩት የጦሩ አባሎች ምትክ ከስር ከስሩ በአጭር ጊዜ ስልጠና ከየገጠሩ ያልተማሩትን እየመለመለ ወደ ተለያዩ የጦር ክፍሎች እየመደበ ሲሆን በቀጣይም የማባረሩ ዘመቻ በስፋት የሚቀጥል መሆኑንም ከምንጮቹ ገለጻ ለመረዳት ተችሎዋል።ምንም ያልተማሩትን ከገጠር እየመለመለ በጦላይ የጦር ማሰልጠኛ፤በሁርሶ የጦር ማሰልጠኛ እና በሌሎችም በድብቅ አሰልጥኖ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ሰራዊቱ እየመደበ መሆኑም ታውቆዋል።

በተለይ በምእራብ እዝ ሰሞኑን የተሰናበቱት ነባር የሰራዊቱ አባሎች ያነጋገረው እና የስንብት ደብዳቤና መታወቂያ የሰጠው የምዕራብ እዝ የአስተዳደር እና ፋይናንስ ምክትል ኃላፊ የሆነው ብ/ጀ/ል ጌታቸው ሽፈራው ሲሆን በወቅቱ ባደረገው ንግግር « እስከ አሁን ያበረከታችሁት አስተዋፅ ቀላል አይደለም ።ወደፊትም እናት ሀገራችሁ ስትፈልጋችሁ ጥሪ ታቀርብላችሁዋለች ስለዚህ ቅሬታ እንዳይሰማችሁ።በቀጣይም እኛም የናንተው እጣ ሊደርሰን ይችላል» ብሎዋል። ብ/ጀ/ል ጌታቸው በሚሰራበት ቦታ ላይ ከበላይ ከፍተኛ ጫና እየደረሰበት መሆኑንና በቀጣይም የመባረር እጣ እሱም ሊደርስበት እንደሚችል ለተባረሩት የጦሩ አባላት በገደምዳሜ የገለፀ ሲሆን በወያኔ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ላይም እነ መለስ ዜናዊ ጥርጣሬና ስጋት እንዳላቸው እና ምንጠራው በነሱ ላይ ቀጣይ እንደሆነ አመላካች ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል።

በቅርቡ ከተቃዋሚ ታጣቂ ኃይሎች ጋር ወግነዋል፤መፈንቅለ መንግስት ሙከራ አድርገዋል፤ ከፍተኛ ባለስልጣናትን ለመግደል አሲረዋል ፤የመንግስት ተቋሞማትን ለማፍረስ ሙከራ አድርገዋል እያሉ ሰበብ እየደረደሩ ለእስር የዳረጉዋቸው ከፍተኛ መኮንኖች ቁጥራቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ የመጣ መሆኑንና ሂደቱም የሰራዊቱን አባሎች ለማስደንገጥ ብሎም አንገት ለማስደፋት ሆን ብለው መለስ ዜናዊና ግብረ አበሮቹ የሸረቡት ሴራ ነው ሲሉም ምንጮቹ ገልፀዋል።

80 ያህል ግዙፍ ድርጅቶች ከአፍሪካ በግንባር ቀደም የሆኑ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ለመመስረት እና በበላይነት መለስ ዜናዊ እየተቆጣጠረ ለመስራት

ምስጢራዊ ስምምነት የተደረገ ሲሆን ከነዚህ ግዙፍ ኩባንያዎች መሀከል የመጀመሪያ የሆነው የመስታወት ፋብሪካ  በመለስ ዜናዊ ተመርቆ ስራ መጀመሩ ታውቆዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ፓርቲው እና ባለስልጣናቱ ሳያውቁ በድብቅ እና በምስጢር ከቻይና ባለስልጣናት እና ከቻይና ባለሀብቶች ጋር ምስጢራዊ ስምምነት ከአንድ አመት በፊት የተፈራረሙ ሲሆን በዚሁ ስምምነታቸው ላይ የቻይና ባለሀብቶች እና ባለስልጣናት ከኢትዮጵያ ምቹ ቦታና ልዩ ጥበቃ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ  ነገሮች የሚደረጉ ሲሆን ከቻይና በኩል ደግሞ መለስ ዜናዊ ኩባንያዎቹን በበላይነት እንዲመራና እንዲቆጣጠር በማለት የአክስዮን ማህበር ውስጥ ማስገባታቸው ታውቆዋል::

ከዚህም ስምነት መሀከል አንዱ የሆነው የመስታወት ፋብሪካ ሰሞኑን በራሱ በመለስ ዜናዊ ተመርቆ ስራ የጀመረ ሲሆን እስከ አሁን በአፍሪካ አሉ ከተባሉት ፋብሪካዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

አምባገነኑ መለስ ዜናዊ በፀረ ሽብርተኛ ስም ከአሜሪካ እና ከእንግሊዝ መንግስታት ከፍተኛ የገንዘብ እና የቁሳቁስ ድጋፍ ሲደረግለት የነበረ ሲሆን ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ግን ነገሮች በመለወጣቸው በተለይ የወያኔ ቡድን ሰው በላና ጨፍጫፊ መሆኑን ሲረዱ ድጋፉን ከማቋዋረጣቸውም በተጨማሪ በሰብአዊ መብት ጥሰት እየወነጀሉ በመሆናቸው ፊቱን ወደ ቻይና በማዞር ከፍተኛ ትስስር እንደፈጠሩም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በመሆኑም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና ቡድኑ በአሁኑ ሰዓት ከቻይና ጋር አዲስ ፍቅር የጀመሩ ከመሆኑም በላይ ከፍተኛ ትስስር ላይ በመድረሳቸው ጥቃቅን የሚባሉ እቃዎችን ሳይቀር ከቻይና በውድ ዋጋ እያስመጡ ሀገሪቱዋን የቻይና ሸቀጥ ማራገፊያ ከማድረጋቸውም በተጨማሪ በሀገር ውስጥ ያሉ የግንባታ ፕሮጀክቶች ሙሉ ለሙሉ ለቻይና ተሰጥተው መለስን ጨምሮ ጥቂት ባለስልጣናት ከፓርቲያቸው እውቅና ውጭ ኮሚሽን እየተከፈላቸው መሆኑም ዘገባው አብራርቶዋል::

አምባገነኑ የወያነው መሪ መለስ በምስጢር ከቻይና ባለስልጣናት እና ባለሀብቶች ጋር የተፈራረሟቸው የንግድ ዘርፎች የቆዳ፤የቀለም፤የመኪና፤የመስታወት፤የእርሻ እና ሌሎችም ሲሆን ኩባንያዎቹ ስራ ሲጀምሩ በበላይነት የሚመራው እና የሚቆጣጠረው መለስ እንዲሆን በስምምነታቸው ላይ በመስፈሩ ሰሞኑን የተከፈተውን የመስታወት ፋብሪካ ሚስቱ አዜብ መስፍን መቆጣጠር እንደ ጀመረችም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ሀገርን እና ህዝብን በድህነት አረንቋዋ ውስጥ ነክረው እነሱ አንዴ ቻይና ሌላ ጊዜ ሱዳን እያሉ ከግል የንግድ ሸሪኮቻቸው ጋር በመመሳጠር የህዝብ ሀብት እየቦጠቦጡ ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱን ለድህነት ህዝቡዋን ለባርነት ለመዳረግ ለባዕድ አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ መሆኑንም  ዘገባው ገልጾዋል::

ባለፈው ሳምንት በደረሰን ዘገባ መሰረት ከኢትዮጵያውያን አርሶ አደሮች ላይ ተነጥቆ ለሱዳን ባለሀብቶች ተቆርሶ በተሰጣቸው ለም መሬት ላይ ያለሙትን ቀይ ሽንኩርት፣ነጭ ሽንኩርት፣ድንች፣ እና ሌሎችም የጉዋሮ አትክልቶች በ50 የጭነት መኪናዎች ጭነው ወደ መሀል ሀገር እስከ አዲስ አበባ ድረስ አስገብተው የሸጡ ሲሆን ከዚህም የተለያዩ ሸቀጦችን በርካሽ ዋጋ እየገዙ ያለ አንዳች ከልካይ እንደልባቸው እያመላለሱ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ ገልያዋል፡፡

የሀገሪቱን ባለሀብቶችና ነጋዴዎች ከንግዱ አለም ለማስወጣት የወያኔ ኩባንያዎች እየሰሩ ከመሆኑም በላይ አሁን ደግሞ ይባስ ብለው የሱዳን ባለሀብቶች በተለያዩ የንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው ያለምንም ቀረጥ እና ግብር ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ድንበር አቋዋርጠው እየገቡ እንደልባቸው እየነገዱ መገኘታቸው ወያኔ ነጋዴውን ህብረተሰብ ለማሽመድመድ እና ከውድድር ውጭ ለማድረግ የዘረጋው ስልቱ መሆኑንም ዘገባው አብራርቶዋል፡፡

ዛሬ ሀገሪቱዋ ከምትችለው አቅም በላይ በየአመቱ ለጅቡቲ ወደብ እየከፈለች በመሆኑ ህዝብና ሀገር ለከፍተኛ ችግር ተጋልጠው እንደሚገኙና በተለይ የንግዱ ህብረተሰብ ለከፍተኛ ኪሳራ እንዲዳረግ ሆን ብለው እያውጠነጠኑ መሆናቸውን ያሳያል ሲል የደረሰን ዘገባ ገለፀ፡፡

በቅርቡ የጅቡቲ መንግስት የወደብ ታሪፍ ጭማሪ ማሻሻያ አድርጌያለሁ በማለት በአንድ ወር ብቻ የ22 ሚሊዮን ብር በላይ ቀደም ሲል ሲከፈል ከነበረው ተጨማሪ አድርጎ የነበረ ሲሆን በዚህም ሳያበቃ ደግሞ እንደገና ሰሞኑን ሌላ ምስጢራዊ የወደብ ታሪፍ ጭማሪ ማድረጉዋ ተጋልጦዋል፡፡በዚህም የተነሳ የሀገሪቱዋ ነጋዴዎች በተደረገባቸው የወደብ ታሪፍ ጭማሪ አቅም እያነሳቸው እና እየደከሙ የሚከፍሉት በማጣታቸው ያስመጡት እቃዎች እየተወረሱባቸው መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልጸ የወያኔ ባለስልጣናት ለህዝብና ለሀገር የሚል ቅንጣት ታክል ማሰቢያ የሌላቸው ለራሳቸው ብቻ ከውጭ ሀገር ባለሀብቶች ጋር ተመሳጥረው እያግበሰበሱ ነጋዴውን ወደ ጎን አድርገው እያገለሉት መሆኑም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል፡፡